የሰ/መ/ቁጥር 230249

መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ/ም

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**
**ሰበር ሰሚ ችሎት**

ዳኞች ፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ብርሃኑ አምዴ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ዘነበች ሃይሉ ጠ.ዳኛው ተሊ. - ቀረቡ

2ኛ. ወ/ሮ ሰላማዊት ሃይሉ

3ኛ. ወ/ሮ ታደለች ኃይሉ } ጠ.ትሁት መንገሻ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የውርስ እዳ እንዲከፈል የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የሰበር ቅሬታ የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 210445 በሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

አመልካች በግንቦት 09 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ተጠሪዎች የሟች የአቶ ጌታቸው ሃይሉ እህቶችና ህጋዊ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው፡፡ የሟች አቶ ጌታቸው ሃይሉ የውርስ ንብረት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 110067 ተጣርቶ በሐምሌ 11 ቀን 2006 ዓ.ም ጸድቋል፡፡ ሟች

በመጋቢት 07 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል በተወካያቸው በ1ኛ ተጠሪ በኩል ከአቶ ሰለሞን ከበደ ብር 700,000.00 ተበድረዋል፡፡ ይህንንም የብድር ገንዘብ አቶ ሰለሞን ደበበ ግንቦት 29 ቀን 2006 ዓ.ም ባደረጉት የስጦታ ውል ለአመልካች አስተላልፈዋል፡፡ ብድሩ በውርስ እዳነት በውርስ ማጣራት ሪፖርት ውስጥ ፀድቋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የሟች ወራሽ በመሆናቸው አበዳሪው በስጦታ ለአመልካች ያስተላለፉትን የብድር ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በአንድነትና በነጠላ ከህጋዊ ወለዱ ጋር ለአመልካች እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በጥቅምት 27 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ለሟች አቶ ጌታቸው ሀይሉ ተወካይ በመሆን የብድር ውሉ ላይ አልፈረምኩም፡፡ ብር 700,000.00 አልተበደርኩም፡፡ የቀረበው የብድር እና የስጦታ ውል ሰነድም ሃሰት ነው፡፡ የስጦታ ውሉ ሲደረግ አበዳሪ ሟች አቶ ሰለሞን ራሱን በማያውቅበት በከፍተኛ ህመም ወስጥ ነበረ፡፡ አመልካች ሆን ብለው ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ያደረጉት ስለሆነ ልከፍል አይገባም ያሉ ሲሆን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው የብድር ውሉ ላይ አልፈረምንም በመሆኑም ልንከፍል አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ተጠሪዎች ከውርስ ሀብቱ ላይ ብር 700,000.00 ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ 1ኛ ተጠሪ በብድር ውሉ ላይ ሟች አቶ ጌታቸውን ሃይሉን ወክለው ለመፈረማቸው ክደው የተከራከሩ በመሆኑ በፎረንሲክ እንዲመረመር ያዘዘ ቢሆንም በፎረንሲክ ምርመራ ሊጣራ ባለመቻሉ በብድር ውሉ ላይ የተጠቀሱ ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ በእነዚህ ምስክሮች በብድር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ እንዲሁም አበዳሪ አቶ ሰለሞን አበበ ለሟች ወኪል ወ/ሮ ዘነበች ኃይሉ መጋቢት 12 ቀን 2003 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ያበደሩትን ገንዘብ ለአመልካች በቀን 29/09/2006 በስጦታ መልክ ያስተላለፉላቸው ለመሆኑ የስጦታ ውል አቅርበዋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ብር 700,000.00 ከሰኔ 29 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለአመልካች በድርሻቸው ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በስር ፍርድ ቤት የተሰሙ ምስክሮችን ቃል እንደገና በመመዘን አመልካች የብድር ውል ሰነድ ነው በማለት ያቀረቡት ሰነድ ላይ ሟች አቶ ጌታቸውን ወክለው 1ኛ ተጠሪ መፈረማቸውን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ምስክሮች ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ እና መሰረታዊ ልዩነት እያለበት ነው፡፡ እንዲሁም ተጠሪዎች የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ገንዘቡ የውርስ ሀብት እዳ ተብሎ መመዝገቡን የተቃወሙ በመሆኑ አመልካች ሟች አቶ ጌታቸው ሀይሉ ከአቶ ሰለሞን ደበበ ላይ ብር 700,000 መበደራቸውን በተገቢው ማስረጃ አስረድተዋል ሊባል አይችልም በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ ተጠሪዎች የውርስ እዳ የተባለውን ብር 700,000.00 ከውርስ ሀብቱም ሆነ ከራሳቸው ለመክፈል አይገደዱም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ የቅሬታው ይዘት ተጠሪዎች በሟች አቶ ሰለሞን ኃይሉ የተደረገውን የብድርም ሆነ የስጦታ ውል እንዲፈርስ የዳኝነት ከፍለው ክስ ባላቀረቡበት ሁኔታ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሉ ፈራሽ እንዲሆን መወሰኑ፣ የብድር ውል ለመደረጉ ምስክሮቹ በበቂ ሁኔታ የመሰከሩ ቢሆንም ከውሉ የጊዜ ርዝመት አኳያ ውሉ የተደረገበትን ቦታና እና ውሉ እንዴት እንደተፃፈ በመርሳት የሰጡት ቃል በውሉ ላይ መሰረታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ መቁጠሩ፣ በፍ/ሕ/ቁጥር 2005 መሰረትም በጽሁፍ የተደረገው ውል በራሱ በቂና በምስክር የማይተባበል ሆኖ እያለ ይህ ከግንዛቤ ሳይገባ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት የለውም መባሉ፣ የተጠሪዎች ጠበቃ የብድር ውሉን ተቀብለውና አምነውበት ብድሩ የውርስ እዳ መሆኑን በማረጋገጥ ሪፖርቱ ጸድቆ እያለ፣ በስር ፍርድ ቤት የመሰከሩት አንደኛው ምስክር የ1ኛ ተጠሪ አጎት በመሆናቸ ተጠሪዎችን ለመጥቀም በማሰብ ውሉ የተደረገበትን ቦታ እና አፈራረማቸውን ሆን ብለው በማዛባት በሰጡት የምስክርነት ቃል ላይ ተመስርቶ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የብድር ውሉ ውድቅ እንዲሆን ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካችን ቅሬታ መርምሮ ለክርክሩ መሰረት የሆነው የብድር ገንዘብ የሟች አቶ ጌታቸው ሀይሉ የውርስ ሐብት በተጣራበት ጊዜ የውርስ ሐብት እዳ ሆኖ ሲመዘገብ ተጠሪዎች ባልተቃወሙበት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የመሻሩን አግባብነት ለማጣራት ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ አዟል፡፡

ተጠሪዎች በጥቅምት 10 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች ባዘጋጁት የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ አስተያየት ባልሰጠንበት አከራካሪው ገንዘብ በእዳነት በመመዝገቡ ብቻ ተጠሪዎች በእዳው እንደተስማማን ሊቆጠር አይችልም፡፡ የብድር ሰነዱን ክደን በመከራከራችን በፎረንሲክ ምርመራ ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ በብድር ውሉ ላይ የተጠቀሱት ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡ የምስክሮቹ ቃልም መሰረታዊ ልዩነት ያለበት እና እርስ በእርሱ የሚጋጭ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በህዳር 02 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፣ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ሟች ጌታቸው ሐይሉ በተወካያቸው በ1ኛ ተጠሪ በኩል የተበደሩትን ገንዘብ ተጠሪዎች የሟች ወራሾች በመሆናቸው እንዲከፍሏቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ክስ ያቀረቡበትን

የብድር ገንዘብ ሚች መበደራቸውን ለማስረዳት የብድር ውል እና በሐምሌ 11 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ የጸደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች የብድር ውሉን ክደው በመከራከራቸው በተለይም 1ኛ ተጠሪ በብድር ውሉ ላይ ሚችን ወክለው ያልፈረሙ መሆናቸውን ክደው በመከራከራቸው ጉዳዩ የተጀመረበት ፍርድ ቤት በብድር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የ1ኛ ተጠሪ ስለመሆኑ በፎረንሲክ ምርመራ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ በብድር ውሉ ላይ ያለውን ፊርማ መመርመር የማይቻል መሆኑ መርማሪው አካል ለፍርድ ቤቱ አሳውቋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህንን ተከትሎ በብድር ውሉ ላይ የተቆጠሩ ምስክሮችን ሰምቷል፡፡ በመሆኑም የብድር ውል መኖር ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ የምስክሮች ቃል መስማቱ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

በመሰረቱ ከብር 500 በላይ የሆነ የብድር ገንዘብን ለማስረዳት ሊቀርብ ስለሚገባው የማስረጃ አይነት በፍ/ሕ/ቁጥር 2472/1 ላይ የተዘረዘረ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ የብድር ግንኙነት መኖሩን ማስረዳት የሚቻለው በጽሁፍ፤ ወይም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም በመኃላ ቃል ብቻ ነው፡፡ የብርድ ውል መኖሩን ለማስረዳት ከእነዚህ ሌላ የማስረጃ አይነት ማቅረብ እንደማይቻል ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የብድር ውል በማስረጃነት ያቀረቡ ቢሆንም ፊርማው ስለተካደ እና በሳይንሳዊ ዘዴ ፊርማው የ1ኛ ተጠሪ መሆኑን ማረጋገጥ ስላልተቻለ አመልካች ያቀረቡት የጽሁፍ የብድር ውል ማስረጃ ሊሆን አይችልም፡፡ በጽሁፍ የተደረገ የብድር ውል ላይ ያለ ፊርማ በተካደ ጊዜ የብድር ውል በጽሁፍ መደረጉን በምስክሮች ማረጋገጥ የሚቻል ስለመሆኑም የፍ/ሕ/ቁጥር 2472 አያመለክትም፡፡ ይልቁንም በፍ/ሕ/ቁጥር 2472/2 ለብድር ውል ሌላ ማናቸውንም ማስረጃ ማቅረብ አይቻልም ማለቱ የብድር ውል በተካደ ጊዜ በብድር ውሉ ላይ የተቆጠሩ ምስክሮችም ቢሆን የብድር ውል ስለመደረጉ ማስረጃ ሊሆኑ እንደማይችሉ አመላካች ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የምስክሮችን ቃል መዝነው የደረሱበትን ድምዳሜ አግባብነት መመርመር ሳያስፈልግ የብድር ውል መኖሩን ለማረጋገጥ በስር ፍድ ቤቶች የምስክር ቃል መስማቱ በራሱ የፍ/ሕ/ቁጥር 2472 ን የሚቃረን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሌላው አመልካች ሚች በብድር የወሰዱት ገንዘብ መኖሩን ለማስረዳት ያቀረቡት የሚች የውርስ ሐብት ተጣርቶ ሪፖርቱ የጸደቀበትን ውሳኔ ሲሆን በሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ተጽፎ በቀረበ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ የሚች የውርስ ሐብት እዳ ተብሎ ብር 700,000.00 የተመዘገበ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ይህን የውርስ አጣሪ ሪፖርት ተጠሪዎች ሳይቃወሙ የጸደቀ መሆኑንም የውርስ ሐብቱ የተጣራበትን መዝገብ አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን የውርስ አጣሪ ሪፖርት በማጽደቅ የተሰጠ ውሳኔ እንደ አንድ ማስረጃ የሚታይ በመሆኑ ይህ የውርስ አጣሪ ሪፖርት የብድር ውል መኖሩን ለማስረዳት ሊቀርብ ይችላል ወይ? የሚለው ከፍ/ሕ/ቁጥር 2472/1 አኳያ የሚታይ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የብድር ገንዘብ እንዲከፈላቸው ክስ ሲያቀርቡ ተጠሪዎች የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ በእዳነት መመዝገቡ ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ በመሆኑ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱም የብድር ገንዘብ ስለመኖሩ ማስረጃ ሊሆን አይችልም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የብድር ገንዘብ እንዲከፈላቸው በጽሁፍ የተደረገ የብድር ውልን እና የውርስ አጣሪ ሪፖርትን መሰረት አድርገው ክስ ያቀረቡ ቢሆንም የብድር ውሉ ላይ ያለው ፊርማ የተካደ እና በምርመራ ማረጋገጥ ያልተቻለ በመሆኑ አመልካች በፍ/ሕ/ቁጥር 2472/1 መሰረት የብድር ውል መኖሩን የሚያስረዳ በህጉ ተቀባይነት ያለው ሌላ ማስረጃ ማለትም በፍርድ ቤት በተደረገ የእምነት ወይም የመሐላ ቃል ማስረዳት አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል መመዘኑ ተገቢ ባይሆንም ከውጤት አንጻር የብድር ገንዘብ መኖሩ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 210445 በሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የነበረው ክርክር ያስከተለውን ወጪ ግራቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ትእዛዝ

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 110067 በመጣበት አኳኋን ተመላሽ ይደረግ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*